ህግ *(1982: 316)* የሴቶች ግርዛት ይከለክላል

# INFORMATION OM KÖNSSTYMPNING

*Amhariska*

Sweden

# ግርዛት

**በስዊድን ሕግ (SFS 1982:316) መሰረት የሴቶች ግርዛት የተ ከለከለ ነዉ።**

ግርዛቱ ከስዊድን ዉጪ እንኳን ቢኪያሄድ ይህንን ሕግ የሚጥስ ሰዉ እስከ 10 ዓመት የሚደርስ እስራት ይፈረድበታል። ግርዛት ለመፈ ፀም መሞከር፣ መዘጋጀት እንዲሁም ሌላ ሰዉ ግርዛቱን እንዲፈፅም ማሳመን ሕገወጥ ነዉ። ግርዛት እንደሚፈፀም እያወቁ አለማመልከ ትም ሕገ ወጥ ነዉ። ግርዛቱን እሚፈፅመዉ ሰዉ ማንም ቢሆንም እንኳን የሴቶቹ ወላጆች የማስቆም ሓላፊነት ኣለቸዉ እንዲሁም በስዊ ድን በወንጀል ሊከሰሱ ይችላሉ።

ህግ *(1982: 316)* የሴቶች ግርዛት ይከለክላል

LÄNSSTYRELSEN
ÖSTERGÖTLAND

Polisen

# የሚያስከትለው ጉዳት

**የሴቶች ግርዛት ማለት የሴቶችን ዉጫዊ ሀፍረተ ስጋ ለመቀየር ወይ ለመ ጉዳት ያለመ ጥቃት ነዉ። የሴቶች ግርዛት በተለያየ መንገድ ጉዳት ሊያደ ርስ ይችላል እንዲሁም ወድያዉኑ ወይ በቀጣይ ሂወት ላይ የሚከተሉትን ጉዳቶች ሊያደርስ ይችላል፡**

- በሂደቱ ግዜ ከባድ ደም መፍሰስ
- ኢንፌክሽኖች
- በሃፍረተ ስጋ አካባቢ ህመም
- ለመሽናት መቸገር
- የወር አበባ ግዜ መቸገር
- በፆታዊ ግንኙነት ግዜ ለሴቷና ለወንዱ ስቃይ
- ሴቶች እንዳይወልዱ ጉዳት ማድረስ
- በወሊድ ጊዜ ችግር ይፈጠራል
- የአእምሮ ችግር
- ሞት

# የግርዛት ዓይነቶች

**WHO አራት ዓይነት ግርዛት እንዳለ ይገልፃል፡**

**ዓይነት 1:** ቂንጥሩ ወይ የቂንጥሩ አካባቢ ይወገዳል።

**ዓይነት 2:** የቂንጥሩ ዉስጣዊ ከንፈርና (ዉስጣዊ ላቢ) አንዳአንዴ ዉጫዊ ከንፈር (ዉጫዊ ላቢ) ይቆረጣል።

**ዓይነት 3:** የቂንጥሩ ዉስጣዊ ከንፈርና (ዉስጣዊ ላቢ) ዉጫዊ ከንፈር (ዉጫዊ ላቢ) ተቆርጦ የሀፍረተ ስጋ ክፍተት ለመ ሸፈን አንድ ላይ ይሰፋል።

**ዓይነት 4:** እንደ መዉጋት የመሳሰሉ ሌሎች ሀፍረተ ስጋ ሂደቶች።

ስለ ተለያዩ ዓይነት ግርዛት ሲወራ አንድአንዴ «ሱናህ» ይነሳልለ። ሁሉም የግርዛት ዓይነቶች «ሱናህ» ጨምሮ ሕገ ወጥ ናቸዉ!

Polisen

LÄNSSTYRELSEN
ÖSTERGÖTLAND

ህግ *(1982: 316)* የሴቶች ግርዛት ይከለክላል

*Detta material är framtaget av Länsstyrelsen Östergötland.*